# ደምር መጣ ደሞ!



ለሁለተኛው ዙር ጥርጊያ ተዘጋጅቶ፣
የሱስ ወንድም ደምር ይኸው መጣ ደሞ።

በመጀመርያው ዙር ሰውን ጥንብዝ አርጎ፣
ይጦብያ ሱስ ናት ሕዝብን አደንዝዞ፣
ወንበር አግዳሚውን ወሰደ ጠራርጎ።

የሱስ ወንድም ደምር ዓይን አውጣው ቀበሮ፣
ሲከፍል ሲቀንስ ሲበታትን ኖሮ፣
ጣድቅ መስሎ መጣ ደማሪ ነኝ ብሎ!

ደማሪ አዋሃጁን ሲያስገርፈው ባጅቶ፣
እያነፈነፈ ስልክ ጆሮ ጠብቶ፣
ንስሃ ሳይገባ ይሁዳ ዘ አስቆርቶ፣
ስንቱን አጃጃለው ምላሱን አትብቶ!

ትናንትናም ዛሬም ደጋግሞ እንደታየው፣
ወላዋይ ቀላማጅ ጎጋውና መንጋው፣
ይሁዳም ተነስቶ መስቀልን ቢሰብከው፣
“መደመር!” እያለ እሚያዳምጠው ነው።

ሰልሎና አቃጥሮ እግር ያስቆረጠ፣
ወንዶችን ለማምከን ብልት ያሰለብ፣
ልጆችን ያላባት ሜዳ ላይ ያስቀረ፣
ወላጅ ያለ ጧሪ ሲያስለቅስ የኖረ፣
መች ሱባዔ ገብቶ መስቀል ተሸከመ?

ከእጁ ላይ ያለን ደም በንስሃ ሳያጥብ፣
በካድሬ ምላሱ መደመርን ሲያነብ፣
ሰማእት ረስቶ የሚከተለው ህዝብ፣
የሞቱት ቢነሱ እንዴት ያስተዛዝብ!

በይህ አድግ ባሩድ ተወግቶ ላለቀው፣
በይህ አድግ ምጣድ እንደ ኑግ ላረረው፣
በይህ አድግ ጭካኔ እግሩን ዓይኑን ላጣው፣
በይህ አድግ ክፋት ተሰልቦ ለኖረው፤
ጆሮ ጠቢው ቀርቶ ተጠያቂው ማነው?

እርጉሙን ተቅዱስ እያለ ደምረው፣
ነፍስ አጥፊን ተሟቹ እያለ ቀላቅለው፣
ዘራፊን ተጨዋ እያለ አገናኘው፣
ፍየሉን በጉንም እንደ አህያ ነዳው!

መቼም ትምህርት የለ ዘንድሮም እንዳምናው፣
ስንት ጂላጅል ሕዝብ በሱስ ሊጠረግ ነው!

ሱሱን ጭልጥ አርጎ ሕዝብ ሲያንቀላፋ፣

ግንዱን አንከባሎ ተላይ ተሱሉልታ፣
ጉልት አደረገው ታዲሳባ ጫንቃ።

እየዋለ ሲያደር ሱሱ ሲጠንክር፣
ያፈናቅል ጀመር ዜጋ እንደ ባይተዋር።

የሱስ ማደንዘዣ አገር አስተኝቶ፣
ጋሞን አስጠረገ ሸዋ ውስጥ ቡራዮ።

ሱሱ ከቡራዮ እንደ ጎርፍ ፈሶ፣
ጠቅልሎ ወሰደው "መጤን" ለገጣፎ።

ስካር የነዳው ሱስ ስብተን በጥሶ፣
የእንጦጦን አቀበት ሽቅብ ተፈናጦ፣
ሱሉልታን አወከው ውሀ ሙላት ሆኖ።

የመደመር ጥበብ ወደ ደቡብ ነጉዶ፣
በማበል ወሰደው ጌዲኦን ጠራርጎ።

ሱስና መደመር አንድ ላይ ተጣምረው፣
አዲስባን አፍሰው ጠርገው ሊወስዱት ነው።

መንጋውን አንደሆነ ዛሬም ስናጤነው፣
ይሁዳም ተነስቶ መጣፍ ጥፎ ቢያየው፣
መስቀል መደመር ነው እያለ ቢሰብከው፣
አሜን አሜን ብሎ የሚሰግድለት ነው!

ሰው ከንቱው!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.